# የወረርሽኝ ስራአጥነት እርዳታ (PUA)

# በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች (FAQ's)

**የመጨረሻ እርምት፡ 5/13/2020**

የፌደራል ኮሮናቫይረስ ድጋፍ፣ እርዳታና የኢኮኖሚ ዋስትና (CARES) ደንብ እንደ ሕግ የተፈረመው ማርች 27, 2020 ነው፡፡ ይህ ደንብ የተሻሻለ አንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንስ (UI) ጠቀሜታና የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ለኔቫዳ ሰራተኞች ያቀርባል፡፡ ማወቅ የሚያስፈልጋችሁ ዝርዝር ይኸው፡፡

## የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ ምን ማለት ነው (PUA)?

የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA)፣ አዲስ፣ ጊዚያዊ የሆነ የፌደራል ኮሮናቫይረስ ድጋፍ፣ እርዳታና የኢኮኖሚ ዋስትና (CARES) ሕግ አካል ነው፡፡ የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ከፌብርዋሪ 2, 2020 እስከ ዲሰምበር 26, 2020 ድረስ ይቆያል፡፡ የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ለዚህ ፕሮግራም የወጣውን መመዘኛ አሟልተው ሆኖም ግን መደበኛ አንኢምፕሎይመንት ኢንሱራንስ(UI)፣ የጊዚያዊ ወረርሽኝ ስራአጥነት መደጎሚያ (PEUC) ወይም የስቴት የተራዘመ ድጋፍ (SEB) ለሌላቸው እንዲሁም በስቴት አንኢምፕሎይመንትሕግ መስራት እየቻሉና ለመስራት ዝግጁ ሆነው እያሉ ግንጭራሽ ስራ የሌላቸው፣ ሙሉ ስራ የሌላቸውና በኮቪድ-19 ምክንያት ሊሰሩ ላልቻሉ ለ 39 ሳምንታት ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) እንደሚገባኝ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

የግል ተዳዳሪ ከሆንክ/ሽ፣ ፓርት ታይም ስራ እየፈለግክ/ሽ ከሆንክ/ሽ፣ ለመደበኛው አንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንስ (UI) ተቀባይነት ካጣህ/ሽ ወይም ደግሞ ለአንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንስ (UI), የጊዚያዊ ወረርሽኝ ስራአጥነት መደጎሚያ (PEUC), ስቴት የተራዘመ እርዳታ (SEB) ሁሉ አመልክተህ/ሽ ተቀባይነት ካጣህ/ካጣሽና በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሳቢያ ችግር ካለብህ/ሽ እርዳታ የማግኘት እድል አለህ//ሽ፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የሚመለከትህ/ሽ ከሆነና ስራ ከሌለህ/ሽ፣ ሙሉ ስራ ከሌለህ/ሽ፣ መስራት ካልቻልክ/ሽ በኮቪድ-19 ሳቢያ ችግር አላብህ/ሽ ማለት ነው፡፡

- ኮቪድ 19 በሽታ እንዳለህ ከተረጋገጠ ወይም የኮቪድ-19 ምልክቶች እይታዩ በሃኪም መታየት ካለብህ/ሽ
- የቤተሰብህ/ሽ አባል በኮቪድ-19 ከታመመ
- የቤተሰብህ/ሽ አባል ወይም ቤተዘመድ በኮቪድ-19 ታመው እርዳታ እያደረግክ/ሽ ከሆነ
- ልጅህ/ሽ ወይም ያንተን/ያንቺን ድጋፍ የሚሻ ቤተ ዘመድ ያንተን/ቺን እርዳታ የሚሻ ከሆነና ት/ቤቱ ወይም መዋያው በኮቪድ-19 ሳቢያ ተዘግቶ ከሆነና መስራት የማትችል/ዪ ከሆነ
- በኮቪድ-19 ሳቢያ ከቤት መውጣት እገዳ ተጭኖብህ/ሽ ወደ ስራ መሄድ ካልቻልክ/ሽ
- ኮቪድ-19 ስላለብህ/ሽና ወይም ኮቪድ-19 አለው ተብሎ ከሚጠረጠር ሰው ጋር ንክኪ ስላለህ/ሽ ሃኪም ራስህን/ሽን እንድታግድ/ጂ ከተመከርክ/ሽ፣ በዚህ ምክንያት ስራ መሄድ ካልቻልክ/ሽ
- አዲስ ስራ ለመጀመር ስትዘጋጅ/ጂ ወይም ስራ ሳይኖርህ/ሽ ቀርቶ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ መሄድ ሳትችል/ዪ ስትቀር/ሪ
- የቤቱ አባወራ በኮቪድ-19 ምክንያት ሞቶ ሃላፊነቱ አንተ/ቺ ላይ ስለወደቀ
- ኮቪድ-19 እንዳለህ/ሽ ስለተረጋገጠና ስራህን/ሽን መስራት ባለመቻልህ/ሽ ከስራ ከወጣህ
- አሰሪ ድርጅቱ በኮቪድ-19 ወረረሽኝ ምክንያት ከተዘጋ
- የግል ተዳዳሪ የነበርክ/ሽ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ስራው በጣም ስለቀዘቀዘ እንድትዘጋ ስላደረገህ

## የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ማግኘት የማይችል ማን ነው?

የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ለማግኘት አንድ ግለሰብ በኮቪድ-19 ሳቢያ ኔቫዳ ውስጥ ስራ የሌለው፣ ሙሉ ስራ የሌለው ወይም መስራት የማይችል ሆኖ ለሌሎች የአንኢምፕሎይመንት እርዳታዎች ተቀባይነት የሌለው መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ ለየወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ማግኘት የማይገባው፡

- ለመደበኛ አንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንስ (UI)፣ የጊዜያዊ ወረርሽኝ ስራአጥነት መደጎሚያ (PEUC), ስቴት የተራዘመ እርዳታ (SEB) ተቀባይነት ያለው/ያላት
- የገቢ ቅናሽ ሳይደረግብህ/ሽ ከቤት መስራት ከቻልክ/ሽ
- ሲክ ሊቭ ወይም ሌላ ሊቭ እየተከፈለህ/ሽ ከሆነ
- በኮቪድ-19 ሳይሆን በሌላ ምክንያት የማትሰራ/ሪ ከሆነ
- በኮቪድ-19 ሳቢያ መስራት ስታቆም/ሚ ኔቫዳ ውስጥ አትስራ/ሪ ከነበር ወይም በኮቪድ-19 ሳቢያ ስራ መጀመር ያልቻልከው/ሽው ኔቫዳ ውስጥ ተጨባጭ የስራ ቅጥር ስላልነበረህ/ሽ ከሆነ

## ለመደበኛ አንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንስ (UI) ወይም ለወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) መመልከት የሚገባኝ መሆኑን በምን እለያለሁ?

ከአሰሪያቸው የ 2019 W2 ያገኙ ሰዎች ወደ ui.nv.gov ወብሳይት በመግባት “File a UI Claim”በመምረጥ ለመደበኛ አንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንስ (UI)በማመልከት ይገባዎት እንደሆን ያረጋግጡ፡፡ ማንም ሰው መደበኛ አንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንስ (UI) የሚገባው ከሆነ ለወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ማመልከት የለበትም፡፡ በኔቫዳ ሕግ መሰረት መሥራት የሚችልና፣ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ፤ ሆኖም ግን በኮቪድ 19 ሳቢያ ስራ ከሌለህ/ሽ፣ ሙሉ ስራ ከሌለህ/ሽ ለመደበኛ አንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንስ (UI) የማይገባው ሰው ለወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ሊገባው/ት ይችል ይሆናል፡፡ለወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ለማመልከት አስቀድመህ/ሽ ለሌሎች አንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንሶች፣ የጊዜያዊ ወረርሽኝ ስራአጥነት መደጎሚያ (PEUC), ስቴት የተራዘመ እርዳታ (SEB) አመልክተህ/ሽ እኒህን እርዳታዎች ማግኘት የመትችል/ዪ መሆን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

## ለየወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) እንዴት ነው ማመልከት የምችለው?

ለዚህ ጠቀሜታ ለማመልከት በኮምፒይተር www.employnv.gov በመግባት የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ማመልከቻ ቅጹን በሞምላት ወይም በስልክ ቁጥር 800-603-9681 በመደወል ማመልከት ይቻላል፡፡ ማመልከቻውን በምትሞሉበት ወቅት የ 2019 ዓመት ገቢዎን ዝርዝር የሚያሳይ ዶኩሜንት በጅዎ ይያዙ፡፡

## ለመደበኛ አንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንስ (UI) አመልክቼ አይገባህም የሚል መልስ አገኘሁ፡፡ በቀጣይ ምን ማድረግ እችላለሁ?

ለመደበኛ አንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንስ (UI) አመልክተው አይገባውም ይተሚል መልስ ካገኙ ሆኖም ግን ለወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) መመዘኛ ነጥቦችን፣ ስራ ከሌለዎት፣ ሙሉ ስራ ከሌለዎት ወይም በኮቬድ-19 ሳቢያ ስራ መስራት የማይችሉ ከሆነ በኮምፒይተር ወይም በስልክ ለወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ማመልከት ይችላሉ፡፡

## ለመደበኛ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (UI) ግን በሂሳብ ስሌት አይገባህም ስለተባልኩ፣ ምን ማድረግ እችላልሁ?

ለመደበኛ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (UI) በሂሳብ ስሌት ማሳወቂያ ለ 0 ሳምንት የሚገባዎት $0.00 የሚል መልስ ካገኙ በኮምፑዩተር ወይም በስልክ ለወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ማመልከት ይችላሉ፡፡

## በጊግ ኢኮኖሚ የምሰራ ወይም የጊግ ሰራተኛ ነኝ፡፡የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ይገባኛል ወይ?

አዎ፣ ገቢውን (ደሞዝ፣ ቲፕ፣ ከስራ ጋር የተያያዘ ገቢ) በተገቢ ሪፖርት ማድረግ የሚችል የጊግ ሰራተኛ ከዚህ በታች ያሉት ነጥቦችን ማሟላት ከቻለ ለየወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ፕሮግራም ሊገባው ይችላል

- በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሳቢያ ስራ ከሌለው፣ ሙሉ ስራ ከሌለው ወይም ስራ ማግኘት ካልቻለና ፈቃደኛ ካልሆነ
- በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሳቢያ ስራህን በሚገባ መስራት ባለመቻልህ ስራህን ካቋረጥክ

## በየወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) የማገኘው እርዳታ ምን ያህል ነው?

የየወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ኔቫዳ የሚከፈለው ዝቅተኛ ሂሳብ $181 ነው፡፡ ሆኖም የ2019 ገቢ ታይቶ እርዳታው ከዚህ በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ከፍተኛው ክፍያ የኔቫዳ ስቴት ለመደበኛ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (UI) ከሚከፍለው $469 ሳምንታዊ ክፍያ በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA)ክፍያ በተጨማሪ ከፌደራል የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት መደጎሚያ በየሳምንቱ $600 ያገኛሉ፡፡ የፌደራል የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት መደጎሚያ በኤፕሪል 4፣ 2020 በሚያልቀው ሳምንት ጀምሮ በጁላይ 25፣ 2020 ማብቂያ ላይ ያቆማል፡፡

## የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ክፍያ በስንት ጊዜ ውስጥ ይደርሰኛል?

ሰራተኞች በሚገባ ሰልጥነው ማመልከቻዎችን እንዲመለከቱ እናደርጋለን፡፡ እያንዳንዱ ማመልከቻ ሳምንታዊ የይገባኛል ማስረጃውን ስለሚመረምር ጊዜ የጠይቃል፡፡መስሪያ ቤቱ በየወቅቱ ወደ ዌብሳይቱ እየገቡ የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ዳድይ የተለወጠ/የተቀየረ ነገር እንዳለ እንዲመለከቱ ይመከራል፡፡ በማመልከቻው ወቅት ክፍያዎ በቀጥታ ወደ ባንክዎ እንዲገባ ወይም ከ 7 - 14 ቀን ሊፈጅ የሚችል ደቢት ካርድ እንዲሆን መምረጥ ይችላሉ፡፡ የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ሰሙናዊ ክፍያ በሜይ መጨረሻ ላይ ይጀምራል፡፡

## ምን ያህል ገቢ አስገባ እንደነበር ለማረጋገጥ ምን ማስረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅብኛል?

ገቢዎን በቶሎ ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢዎን የሚያሳይ መረጃ ይመረጣል፡፡ ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች እንደ W-2, ታክስ ሪተርን፣ የቼክ ክፍያ ቁራጭ፣ የባንክ ደረሰኝ የሂሳብ መዝገብና የእዳ ክፍያ ደረሰኝ ዓይነቶች በቂ ናቸው፡፡ እነህ ዓይነት ማስረጃዎች ማቅረብ ከገቢዎ ጋር በማነጻጸር የሚመደበልዎትን እርዳታ ከፍ ሊያደርገው ይችላል፡ ፡ ማስረጃዎቹ ማመልከቻዎን በሚሞሉበት ጊዜ ማቅረብ ይመረጣል፡፡

## ያለፈውን ገቢየን ለማሳየት ምን ወቅት ማየት ያስፈልጋል?

የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ሰሙናዊንክፍያ ለማስላት የሚያስፈልገው የቅርብ ጊዜ የታክስ ሪተርን ዓመት 2019 ነው፡፡ ከመደበኛ አንኢምፕሎይመንት ኢንሹራንስ (UI) ስሌት ጋር ስለሚለያይ ተጨማሪ ማስረጃ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

## እስካሁን ድረስ ማመልከቻውን መሙላት ባለመቻሌ አሁን ድረስ ላሉ ሳምንቶች ሁሉ መሙላት እችላለሁ ወይ?

DETR የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ወደኋላ ሄዶ ማስላት ስላለበት በኮቪድ-19 ሳቢያ ስራ ካቋረጥክበት ቀን ጀምሮ ያሰላል፡፡ የይገባሃል ውሳኔ ካገኝህ ስራ ካቆምክበት የመጀመሪያው ሳምንት ጀምሮ ክፍያው ይሰጥሃል፡፡ ከፌብርዋሪ 2, 2020 ወደኋላግንሊያልፍ አይችልም፡፡

## የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል?

የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) በኮቪድ-19 ሳቢያ የሚገባህ ከሆነና ከስራ ተፈናቅለህ ከሆነ እስከ 39 ሳምንት ድረስ ይዜዳል፡፡ የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ወቅት ፈብርዋሪ 2, 2020 ሳምንት መጀመሪያ ላይ ጀምሮ እስከ ዲሰምበር 26, 2020 መጨረሻ ድረስ ይቆያል፡፡

## ለወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ጠቀሜታ በየሳምንቱ መሙላት አለብኝ ወይ?

አዎን፡፡ የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ጠቀሚታ ለማግኘት በየሳምንቱ መሙላት ያስፈልጋል፡፡ ሳምንታዊ ማምለከቻው ጉዳይህ በንተልተል ተይዞ ከሆነ ወይም በይግባኝ ላይ ካለ መሞላት ይኖርበታል፡፡ ወደስራ ተመልሰህ የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ክፍያ ካላስፈለገህ ሰሙናዊ ማመልከቻወን ባለማስገባት እንዲቋረጥ ማድረግ ይቻላል፡፡

## በሳምንት ውስጥ ከሰራሁ የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ጠቀሚታየ ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል ወይ?

የሰራኸው ሙሉ ስዓት ካልሆነ፣ በሳምንቱ ውስጥ ምን ያህ ስዓት እንደሰራህ ወይም ምን ያህል ከታክስ በፊት ያስገባህውን ገቢ ሪፖርት ማቅረብ አለብህ/ሽ፡፡ ገቢን ሪፖርት የሚደረገው ሲከፈልህ/ሽ ሳይሆን በስራህው ስዓት የሚከፈልህ መጠን ነው፡ ሰሙናዊ የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ጠቀሜታህ ከታክስ በፊት ገቢህ በ 75% ይቀነሳል፡፡

## የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ጠቀሜታ ታክስ ይቆረጥበታል ወይ?

አዎ፡፡ ማመልከቻህን ስታስገባ እንዲቆረጥ ዋስነህ ከሆነ የታክስ ገንዘቡ ተቀንሶ ይስጥሃል፡፡

## የልጅ ማሳደጊያ ክፍያ ከየወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ጠቀሜታ ላይ ይቆረጣል ወይ?

አዎ፣ የልጅ ማሳደጊያ ክፍያ ልክ ከመደበኛ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (UI)እንደሚቆረጠው ይቆረጣል፡፡

## $600 ለሚከፍለው ፌደራል አንኢምፕሎይመንት መደጎሚያ (FPUC)ይገባኛል ወይ?

ለየወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ተቀባይነት ካገኘህ በየሳምንቱ የሚከፈለውን $600 ይከፈልሃል፡፡ይህን ክፍያ ለማገኘት ምንም ማድረግ የለብህም፡፡ ኤፕሪል 4, 2020 ጀምረው ጁላይ 25, 2020 የሚያቆሙ ሰሙናዊ ሪፖርቶች ሁሉ በየሳምንቱ $600 ያገኛሉ፡፡

## ስርቼ ባላውቅም ለወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ጠቀሜታ ይገባኛልም ወይ?

ከዚህ በታች ያሉትን መመዘኛ ካሟላህ ሊገባህ ይችላል፡

- ስራ ለመጀመር ተዘጋጅተህ በኮቪድ 19 ሳቢያ ስራ ከሌለህ ወይም ወድ ስራ ቦት መድረስ ካልቻልክ
- ቀጣሪህ በኮቪድ-19 ሳቢያ ስራ ካላስጀመረህ
- የቤተሰብህ አባ ወራ በኮቪድ-19 ሳቢያ ከሞተና ሃላፊነቱ አንተ ላይ ከተጫነ

## ከመደበኛ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (UI) ጠቀሜታ አገኛለሁ፡፡ እሱን አቋርጬ ከወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ማመልከት እችላለሁ ወይ?

አይቻልም፡፡ የወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) የሚሰጠው ከቀውጢ ጊዜ ውጭ ለመደበኛ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (UI) ጠቀሜታ የማይበቁ ከሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ግን ብቁ ገቢ ከሌለህ ወይም የመደበኛ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (UI) ማመልከቻህ ላልተወሰነ ጊዜ አይገባህም ከተባልክ ለየወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ጠቀሜታ ሊገባህ ይችል ይሆናል፡፡ ለመደበኛ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (UI) እያመለከትክ እንዲሁም የጊዜያዊ ወረርሽኝ ስራአጥነት መደጎሚያ (PEUC)ና ስቴት የተራዘመ እርዳታ (SEB) እያመለከትክ ከሆነ ለየወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ሊገባህ ይችል ይሆናል፡፡

## ለገቢ ምንጩ ማስረጃ ሊሆን የሚችል ማስረጃ ከሌለኝስ?

የተሟሉ የእርዳታ ማመልከቻዎች ከየወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ብቁ ሆነው ሳምንታዊ $181 በተጨማሪ ከፌደራል አንኢምፕሎይመንት መደጎሚያ (FPUC) $600 ያገኛሉ፡፡ ይህን ገቢ ለማሳደግ ተቀባይነት ያላቸው የገቢ ማስረጃዎች በየወረርሽኝ አንኢምፕሎይመንት እርዳታ (PUA) ወቅት ከቀረቡ በተገቢው የእርዳታ የገንዘብ መወሰኛ ቅጽ ተገልጾ እስከ መጨረሻው ድረስ ይቀጥላል፡፡